# ኤሌክትሪክ የሲጋራ መሣሪያ መጠቀም ጋር የተቆራኘ ከባድ የሳንባ በሽታ



## ማወቅ የሚገባችሁ ነገሮች

አብዛኛዎቹ ግዛቶች፣ ቨርጅኒያን ጨምሮ፣ የ ከባድ ሳንባ በሽታ ምክንያቱ "የ ኤልክትሮኒክ ሲጋራ" *(በ ኤሌክትሮኒክ መሣሪያ ወይም በ ተመሳሳይ እቃ አየር ወይም እንፋሎት ወደ ውስጥ እና ወደ ውጭ መተንፈስ ማለት ነው)* የሚጠቀሙ ታዳጊዎች እና ወጣቶች መሆናቸውን በቅርቡ ሪፖርት አቅርበዋል::

## ምልክቶች

የሚታዩ ምልክቶች ሳል፣ለመተንፈስ መቸገር፣ ለቀናት ወይም ሳምንታት እያደገ የሚሄድ እና ለመተንፈስ የሚያስቸግር ወይም ሆስፒታል ለመሄድ የሚያበቃ ነው:: እንደ ትኩሳት፣ የደረት ህመም፣ ማቅለሽለሽ እና ተቅማጥ ሌሎች ምልክቶች ናቸው::

## በኤሌክትሮኒክ ሲጋራ መጠቀም እና የበሽታው ግንኙነት

በሽተኞች ከመታመማቸው በፊት ለሳምንታት ወይም ለወራት የኤሌክትሮኒክ ሲጋራ መጠቀማቸውን ይናገራሉ:: ይህንን በሽታ የተያዙ ሰዎች የተለያየ አይነት የኤሌክትሮኒክ ሲጋራ መሳሪያዎችን ይጠቀማሉ:: ከበሽታው ጋር የተገናኘ የተለየ መሳሪያ ግን የለም:: ከታማሚዎች አብዛኛዎቹ የተጣራ ወይም ያልተጣራ የማሪዋና ዘይት ይስባሉ:: *("dabbing" ተብሎም ይታወቃል).* የትኛውም የኤልክትሮኒክ ሲጋራ መሳሪያዎችን የሚጠቀም ሰው እነዚህን እቃዎች ከመንገድ ላይ መግዛት የለበትም ወይም አምራቹ ከሚፈቅዳቸው ውጭ የትኛውንም አይነት ንጥረ-ነገር በነዚህ መሳሪያዎች መጨመር የለበትም::

## እንክብካቤን መፈለግ

የከፋ የአተነፋፈስ ስርዓት ህመም የኤሌክትሮኒክ ሲጋራ የሚጠቀሙ ሰዎች አዲስ ችግር ነው:: የኤሌክትሮኒክ ሲጋራ የሚጠቀሙ ታማሚ ሰዎች የመተንፈስ ችግር የሚያጋጥማቸው ከሆነ ወዲያውኑ የህክምና ክትትል ማድረግ አለባቸው::

ወጣቶች የትኛውንም አይነት የኤሌክትሮኒክ ሲጋራ መሳሪያዎች እንዳይጠቀሙ ይመከራሉ እና እነዚህን መሳሪያዎች መጠቀም የሚያመጣው መጥፎ ተፅዕኖ እና የሚያሳየው የጤና ችግር አይታወቅም::

## የአተነፋፈስ ስርዓት ህመም ሪፖርት

የጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች ተጠባባቂ መሆን አለባቸው :: ለከባድ የመተንፈሻ በሽታ ጉዳዮች ከታዳጊዎች እና ወጣቶች መካከል፣ በቅርቡ ስለተጠቀሙት የኤሌክትሮኒክ ሲጋራ መሳሪያዎች መጠየቅ አለባቸው:: እንደዚህ አይነት ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ለአካባቢው የጤና ክፍል ማሳወቅ አለባቸው::

## አሁን አቁሚ ቨርጂኒያ

ማጨስ እና ሌሎች የኒኮቲን ምርቶችን ማቋረጥ የፈለገ ቨርጂኒያዊ በስልክ ወይንም ኦንላይን መረጃ እና ስልጠና ማግኘት ይችላል::
1-800-Quit-Now ደውሉ:: (1-800-784-8669) | www.vdh.virginia.gov/tobacco-free-living/quit-now-virginia/

ኤሌክትሮኒክ ሲጋራዎች ጎጂ ወይም ሊጎዱ የሚችሉ ንጥረ ነገሮችን፣ ኒኮቲን፣ ከባድ ብረት(ምሳሌ ድኝ)፣ ተለዋዋጭ ኦርጋኒክ ውህዶች፣ እና ለካንሰር የሚያጋልጡ ኬሚካሎችን ይይዛሉ:: ወጣት፣ ታዳጊ ወጣቶች፣ እርጉዝ ሴቶች እንዲሁም የሲጋራ ውጤቶችን አሁን ላይ የማትጠቀሙ ወጣቶች የኤሌክትሮኒክ ሲጋራዎችን መጠቀም የለባችሁም:: እነዚህን የኤሌክትሮኒክ ሲጋራዎች ከተጠቀማችሁ፣ ለበሽታ ምልክቶች እራሳችሁን ተቆጣጠሩ (ለምሳሌ ሳል፣ የትንፋሽ ማጠር፣ የደረት ህመም) እና ስለጤናዎ ከተጨነቁ ወዲያውኑ ህክምና እርዳታ ይውሰዱ::

የፌርፋክስ ግዛት፣ ህትመት:: ነሐሴ ,ሁለት ሽህ አስራ ዘጠኝ እ.ኤ.አ ይህ መረጃ በሌላ የፋይል አይነት (ፎርማት) እንዲደርስዎት ለመተየቅ ወደ Fairfax County ጤና መምሪያ በ 703-246-2411, TTY 711 ይደውሉ

ድህረ ገፅ www.fairfaxcounty.gov/health

AMHARIC